


INTERNATIONAL RESCUE COMMITTEE

# የIRC አሰራር ደንብ

ታማኝነት | ተጠያቂነት | አገልጋይነት

## የድርጅታችን የሙያ ስነ ምግባር ደንብ

# ይዘት


የአመራር መልእክት ........ 1

እሴቶቻችን ........ 2

ገዢ መርሆዎች ........ 2

ይህን የስነ ምግባር ደንብ በጥብቅ ለመከተል ያሉብን የጋራ ሃላፊነቶች........ 3

ለስራ ባልደረቦችን የምንሰጠው አትኩሮትና ቁርጠኝነት........ 4

ለደንበኞቻችን ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት........ 6

ለለጋሾቻችን ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት........ 8

ለአቅራቢዎቻችን ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት ........ 10

ለአጋሮቻችን ያለን ትኩረትና ቁርጠኝት........ 12

ለድርጅታችን ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት ........ 14

ለማህበረሰቡ ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት........ 16

እርዳታ ሲፈልጉ........ 18

- የስነ ምግባር አጣብቂኝ ጉዳዮችን መለየት........ 18
- መናገር ያለብዎት ........ 18
- ቅሬታ የሚቀርብባቸው መንገዶች........ 19
- የቅሬታ አቀራረብ........ 20
- የስነ ምግባርና ቅሬታ ማቅረቢያ ነጻ ስልክ መስመር........ 21
- ማንነትን አለመግለጽ እና ሚስጥራዊነት ........ 21
- የፀረ በቀል ፖሊሲ........ 22
- ፈጣን ምላሽ መስጠት ........ 22

ሕግ ማስከበር ........ 23

# የአመራር መልእክት

ውድ ባልደረቦቼ፡

**ይህን ከእናንተ ጋር ስጋራ በደስታ ነው**
**የIRC አሰራር ደንብ፡ የድርጅታችን የሙያ ስነ ምግባር ደንብ**

የIRC አሰራር ደንብ ለረጂም ጊዜ እንደ ስራ ስነ ምግባር ደንብ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ ሲሆነ ሶስቱን ዋና ዋና እሴቶችን ማለትም **ታማኝነት፣ አገልጋይነትና ተጠያቂነት** እና ከእነሱ የሚመነጩ ክንውኖችንን ይገልፃል። እነዚህ እሴቶች እና ተግባራት በመላው አለም የሚገኙትን የIRC ሰራተኞች አንድ የሚያደርጉ እና ከለጋሾቻችን የሚገኘው ሃብት በአግባቡ ተይዞ እንደፍላጎታቸው ፕሮግራሞቻችን የደንበኞቻችንን ደህንነት የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ያደርጋሉ።

የዚህ ሰነድ አላማ ስራችንን በስነምግባር እና በሞራል መርሆዎች በመታገዝ ማከናወናችንን በማረጋገጥ የምናደርገ ውን ሰብአዊ ጥሪ ለማገዝ ነው። ፖሊሲዎች ወደ ተግባር ሊቀየሩ የማይችሉ ከሆነ በራሳቸው ጊዜ በቂ አይደሉም። ለዚህ ነው የስነ ምግባር ደንባችን የሚተገበሩ እርምጃዎችን እንዲያካትት የIRC አሰራር መከተል እንድትችሉ ተደርጎ የተዘጋጀው፤ እንዲሁም ተገቢ ምላሽ ለማግኘት የሚያሳስቡ ጉዳዮች ምሳሌዎች ማጠናከር ያስፈለገው።

የስነ ምግባር መለያው እናንተን በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ባለሙያ ለማድረግ ሳይሆን ስጋቶችን እንድትለዩ፣ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን እንድትይዙ እና የተሻለ ውሳኔ እንድትወስኑ ለመርዳት ነው። ሁልጊዜም በፖሊሲዎችና በአፈጻጸማቸው መካከል ያለውን ክፍተት በንቃት መለየትና ይህንንም ክፍተት ለማጥበብ መስራት ይኖርብናል። ይህ ሰነድ የተዘጋጀው ለIRC ሰራተኞች ቢሆንም ለአጋሮች፣ ለለጋሾች እና ሌሎች አጋዦች በማጋራት የምንገዛባቸውን ደራጃዎች እንዲያወ ቁት ማድረግ ያስፋልጋል።

እባካችሁ ለIRC አሰራር ደንብ ያለንን ቁርጠኝነት እንዲሁም በምናከናውናቸው ተግባራት ሁሉ የIRC እሴቶች ለማስተ ዋወቅ ዝግጁነታችሁን ግለጹልኝ።



ከሠላምታ ጋር፣

**David Miliband**
**ፕሬዚደንት እና ዋና ስራ አስፈጻሚ**




# እሴቶቻችን

### ታማኝነት

ከደንበኞች፣ ከአጋር አካላት፣ ከስራ ባልደረቦች፣ ከለጋሾች እና ከህብረተሰቡ ጋር በግልፅነት፣ በታማኝነትና በእምነት እንሰራለን።

### ተጠያቂነት

በተናጠልም ሆነ በጋራ ለምናሳየው ባህሪ ፣ ድርጊት እና ውጤት ተጠያቂዎች ነን።

### አገልጋይነት

ለምናገለግለው ህዝብ እና አገልግሎቱን እንድንሰጥ ለሚያስች ሉን ለጋሾች ሀላፊነት አለብን።

## ገዢ መርሆዎች

የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል፣ ቀይ ጨረቃ ንቅናቄ እና በአደጋ እርዳታ ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የስነ ምግባር መር ሆዎች ተቀብለናል። በንቅናቄው ዋና ዋና ሰብአዊ መርሆዎች ማለትም ሰብአዊነት፣ አለማዳላት፣ አለመወገን እና ከተጽእኖ ነፃ መሆን በሚሉት እንመራለን።

- **ለአደጋዎች ምላሽ ለስጠት ዋና መነሻችን በአደጋው ከሚጠቁት የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም በጣም ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ሰብአዊ እንግልት እና የመሳሰሉትን መቀነስ ነው። ሰብአዊ ድጋፍ በተፈለገበት ሁሉ ማድረግ ግዴታችን እንደሆነ እንገነዘባለን።**

- **ድጋፋችንን ዘር፣ ሃይማኖት፣ዜግነት የመሳሰሉትን መሠረት ባላደረገ መልኩ እንሰጣለን።ድጋፍም የሚሠጥበት ቅደም ተከተል ፍላጎትን መሠረት ባደረገ መልኩ ነው።**

- **የምናደርገው እርዳታ ለፓለቲካ ወይም ለሃይማኖታዊ አቋም አላማ አይውልም፣ በዚህ መንገድ ለተወሰነ የፓለቲካ፣ የእምነት ወይም የሃይማኖት ቡድን ቃል አንገባም፣ አንሰጥም ወይም እርዳታ አናከፋፍልም።**

- **እንደመንግስት ፓሊሲ ማስፈፀሚያ መሳሪያነት አናገለግልም። እራሳችንን  መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ላልሆኑ አካላት/ሰብአዊ ስራ ከሚሠሩት ዉጪ/፣ ወታደራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን መሠብሰቢያና መጠቀሚያ እንድ ንሆን አንፈቅድም።**

የተባበሩት መንግስታት ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን፣ እናከብራለን፣ እንተገብራለን። የአለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች፣ የሕ ጻናት መብት ስምምነቶችን እና የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሃፊ በወሲባዊ ብዝበዛ እና የተጠቃሚዎች ጥቃት ጥበቃ ላይ የሰጡትን መግለጫ እናከብራለን እንፈጽማለን።

# ይህን የስነ ምግባር ደንብ በጥብቅ ለመከተል ያሉብን የጋራ ሃላፊነቶች

ይህን ደንብ በጥብቅ መከተል የሁሉም የIRCን ተልእኮ ለማስፈጸም የሚሳተፉ አካላት ሁሉ የጋራ ሃላፊነት ነው። ይህ ደግሞ ሁሉንም የIRCን ዳይሬክተሮች፣ ኦፊሰሮች፣ ሰራተኞች፣ "ኢንተርኖች"፣ በጎ ፈቃደኞችበማበረታቻ ክፍያ ብቻ የሚሰሩ ሰራተኞች እና IRCን ወክለው የሚሰሩ አጋሮቻችንን ይመለከታል።

## የተናጥል ሃላፊነቶች

በሥራዎ ላይ የሚተገብሩትን የስነ ምግባር ደንብ በደንብ የመረዳትና የድርሻዎትን የመወጣት ሃላፊነት አለብዎት። የድርሻዎንም እንዲወጡ

- በሥራዎ ላይ ሊተገብሯቸው የሚገቡ የሥነምግባር መርሆዎችን በመማር እንዲሁም ከዚህጋ በተገናኘ የሚሠጡ ስልጠና ዎች ላይ በመሳተፍ **አወቀው ይገኙ**
- ሊወስዱት በሚገባ እርምጃ ወይንም ተግባር ላይ ግልጽ ሳይሆኑ ሲቀሩና ጥርጣሬ ሲኖርዎት **ከሌሎች ምክርና አቅጣጫ ይጠይቁ**
- የስነ ምግባር ደንቦችን እንዳይጣሱና ግቡ እንዲሳካ ጫናዎችን ለቋቋም **ጠንካራ ይሁኑ**
- ትክክል መስሎ ያልተሰማዎት ነገር ሲኖር **ሃሳብዎን ይግለጹ**

## የስራ መሪ ሃላፊነቶች

ሌሎችን የሚመሩ ወይም የሚቆጣቀሩ ከሆነ እምነት ተጥሎብዎ ታል ማለት ነው። የተሰጠዎትን አመኔታ ይዘው ለመዝለቅ ሁልጊዜ ማድረግ ያለብዎ ነገሮች:

- **በምሳሌነት ይምሩ** እንዲሁም ለሌሎች መልካም አርአያ ይሁኑ።
- **የ IRCን የስነ-ምግባር** ደንብ ያሥተዋውቁ (ሌሎች አንዲ ገነዘቡ ያድርጉ) እንዲኑም በስርዎ የሚመሯቸውን ሰራተ ኞች ከደንቡ ጋር ተጣጥመዎ አንዲቀጥሉ የሚያስችላቸውን እውቀትና ግብአት ማግኘታቸውን ያረጋግጡ።
- **በስርዎ የሚመራቸውን ሰራተኞች** ባህሪ ተከታትለው እን ዲሁም በእርስዎ ቁጥጥር ስር ለሚደረገው ማንኛውም እን ቅስቀቃሴ ሀላፊነት ይውሰዱ።
- **ከስነ-ምግባር ወይም አፈጻፀም** ጋር በተያያዘ ለሚቀርቡ ጉዳዩች ፈጣን ምላሽ ይስጡ እንዲሁም ጉዳዩ በአግባብ መንገድ መፈታቱን ያረጋግጡ።





# ለስራ ባልደረቦችን የምንሰጠው አትኩሮትና ቁርጠኝነት

IRC ለሁሉም ሰራተኞች የስራ ደረጃና የስራ ቦታን መሰረት ሳያደርግ ምቹ ፣ ጤናማና ምርታማ የስራ ሁኔታ መኖሩን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው።

## የIRCን አሰራር ደንብ በአግባቡ የሚከተሉት

- ✔ ሁሉንም ሰራተኞች በትህትናና ክብር ሲያስተናግዱ፤
- ✔ ሰራተኛ ሲቀጥሩ  በግለሰብ ችሎታ እና ብቃት አንጂ ከሰራ ጋር ግንኙነት በሌላቸዉ የግለሰቡ ባህርያት መሰረት ሳይሆን ሲቀር፤
- ✔ የሁሉንም ግለሰብ መብት ሰያከብሩ፤
- ✔ የአካል ጉዳተኞች ወይም ልዩ ፍላጎት ያላቸዉን ዜግች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ሲቃወሙ፤
- ✔ ማንኛዉንም አይነት መብት ጥሰት ወይም ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም ሁኔታ ሲቃወሙ፤
- ✔ ስለደህንነት ጉዳይ በቂ መረጃ ሲኖርዎ አካባቢያዊ የደህንነት ህግጋትን ሲከተሉ እና የደህንነት ስጋት ያለበት ስራ ሲያቆሙ፤
- ✔ የግለሰብ መረጃዎችን ሚስጥራዊነት መጠበቅ ሲችሉ።

## ማስወገድ ያለብዎት

- ✗ ግለሰቦችን ከሥራ ጋር ባልተገናኙ ሁኔታዎች መፈረጅ።
- ✗ የሚያንቋሽሹ ቀልዶች፣ የሚያበሳጩ አስተያየቶች፣ የስድብ ኢሜሎች ወይም ወሲባዊ ምስሎች።
- ✗ አልኮል ወይም እፅን ተጠቅሞ ስራን ማከናወን።
- ✗ ባልተገባ ሁኔታ የሰራተኞች መረጃ (የግል መረጃቸዉ ጨምሮ) መግለጽ።

## ሪፖርት ማድረግ ያለብዎት

- ▲ ያልተፈለገ፣ ያልተገባ ወይም ክብር የሚነካ ወሲባዊ ትንኮሳ።
- ▲ መደብደብ፣ የሚያንዣብብ ስጋት፣ ማዋከብ፣ ማዳላት፣ ዝቅ አድርጎ ማየት፣ ማንቋሸሽ የቃል ወይም አካላዊ ቁጣ።
- ▲ የሰራተኞችን ደህነንት አደጋ ላይ የሚጥሉ ሁኔታዎች።
- ▲ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በጾታዊ ባህሪያት፣ በአካል ጉዳት፣ ጡረተኝነት ወይም ሌላ በህግ ጥበቃ በተደረገላቸው ባህሪያት ምክንያት ለግለሰቦች ክፉ መሆን።

# ጥያቄና መልስ

**ጥያቄ:** የስራ ባልደረባዬ ስለ አንዲት ሴት የስራ ባልደባችን አክብሮት በጎደለው መልኩ ሲናገር ሰምቼዋለሁ። ይህን ሚያደርገው ደግሞ ሴቶች በአካባቢው በማይኖሩበት ጊዜ ለመሳቅ ቢሆንም በተደጋጋሚ ያደርገዋል።ይሄ ደግሞ ምቾት አይሰጠኝም።ምን ማድረግ አለብኝ?

**መልስ:** ይህን ለማድረግ የሚመች ከሆነ ግለሰቡ ለብቻው ወስደዉ የሚጠቀምባቸው ቃላት የሚያስከፉ እንደሆኑ ያብራሩለት።ይህን ለማድረግ የማይመች ወይም ከነገሩት በኋላም ባህሪውን የማይቀየር ከሆነ በዚህ የስነ ምግባር ደንብ {እገዛ ያግኙ} በሚለው ክፍል ስር የተቀመጠውን ይከተሉ።

---

**ጥያቄ:** ባለፈዉ ሳምንት ስራ አስኪያጃችን ወደ አንድ ቦታ መስክ ጉዞ እንድናደርግ ጠቀችን ። ወደ ተባለዉ ስፍራ ለመሔድ ቦታዉ ለደህነት ሲባል መታጠሩን በነገርኳት ጊዜ ፡ የሰጠችዉ ሀሣብ በዚያ እኛ እርዳታ የሚያስፈልጋቸዉ ሰዎች ስላሉ መመሄድ እንዳለብን ነዉ።ምን ማድረግ አለብኝ?

**መልስ:** የሰራተኞች ደህንነት ትልቅ ትኩረት የሚሰጠዉ ነዉ። የአካባቢዉ ስምምነቶችም (መመሪያዎች) ይህንን ከግምት ያስገቡ ናቸዉ።የደህንነት ደረጃዎችን ላለመከተል ጫና የሚደረግብዎት ሁኔታ የሚፈጥር ከሆነ በዚህ የስነ ምግባር ደንብ እርዳታ ያግኙ  በሚለዉ ክፍል ስር የተዘረዘረዉን አካሄድ ይከተሉ።

## ጠቃሚ የIRC ፖልሲዎች እና መመሪያዎች:

- እኩል የስራ እድል መስጠት ፖሊሲ
- ከትንኮሳ ነጻ የሆነ የስራ ቦታ ፖሊሲ
- የመስተንግዶ ወጪዎች ፖሊስ
- በስራ ቦታ አደንዛዥ እፅ የመጠቀም ፖሊሲ
- የስራ ቦታ ጥቃት ፖሊሲ
- የIRC አለም አቀፍ ደህንነትና ፀጥታ ፖሊሲ
- የሚስጥር አያያዝ ፖሊሲ
- የደህንነት ፕሮቶኮሎች





# ለደንበኞቻችን ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት

IRC የሚረዳው በግጭት እና በአደጋ ሳቢያ ህይወታቸዉን እና አኗኗራ ቸዉ የጨለመባቸዉ ሰዎች እንዲቋቋሙ፤ እንዲያገግሙ እና ቀጣይ ህይ ወታቸውን እንዲቆጣጠሩ ለማድረግ ነው።እምነት ተጥሎበን የምንሰራው ሰብአዊ ተግባር በክብር መፈፀም ፣ ደህንነታቸውን ማረጋገጥ ደግሞ ቁር ጠኝነታችን ይጠይቃል።

## የIRC አሰራር ደንብ በአግባቡ የሚከተሉት

- ✔ የምናገለግላቸው ሰዎች ክብር፣ እሴቶች፣ ታሪክ እና ባህል ሲያከብሩ፤
- ✔ ደንበኞችን በዘር በእምንት በዜግነት ወይም በሌላ ልዩነት መድልዎ ሳታደርግ ፍላጎትን መሰርት ባደረገና በተቀመጠው የመርህ ግብር ዝርዝር መሰረት ሲመርጡ፤
- ✔ ደንበኞችዎ (ተጠቃሚዎችን) ከወሲብ ጥቃት ሲከላከሉ እና ከሰዎች ህገወጥ ዝውውር እንዲሁም ከማንኛውም አይነት ብዝበዛ ሲታደጉ፤
- ✔ ለህፃናት የተለየ ጥበቃ ሲያደርጉ።
- ✔ በለጋሽ ደንብ መሰረት የመረጃ ጥበቃ ስምምነቶችን እና የደንበኞችን ግላዊ መረጃ አጠቃቀም በተመለከተ ሚስጥራዊነትን ሲጠብቁ።
- ✔ የደንበኞችን ምስል በIRC ኮሙኒኬሽን ስራዎች ላይ በምሚጠቀሙበት ጊዜ ክብሩን ሰብአዊ ፍጡር እንደሆኑ በሚያሳይ መልኩ ሲሆንና ምስልም ሲጠቀሙ የግለሰቡን ፈቃደኝነት አረጋግጠው ሲሆን እንዲሁም።
- ✔ IRC የሚያከናውናቸው ሰውን የሚመለከቱ (የሚያካትቱ) ጥናቶች ከመጀመራቸው በፊት በተገቢው መንገድ ተቀባይነት ማግኘታቸውን ሲያረጋግጡ ነው።

## ማስወገድ ያለብዎት

- ✗ ለIRC ሰራተኞች የሚሰሩ ደንበኞችን በግል መቅጠር (ለምሳሌ የቤት ውስጥ ሰራተኞችን)፤
- ✗ ተጠቃሚዎችን ማዋከብ፣ ማንቋሸሽ፣ ዝቅ ማድረግ እንዲሁም ሌሎች ያልተገቡ ባህሪያት መሳየት፤
- ✗ በደንበኞች ላይ አካላዊ ቅጣት ወይም የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ፤
- ✗ ወሲባዊ ድርጊት ወይም ማንኛውንም አይነት በጣም የቀረበ ግንኙነት በማንኛውም የእድሜ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ተጠቃሚ ጋር ማድረግ፤
- ✗ የሀገሩ ህግ እንኳን ቢፈቅድ በጥቅም እያታለሉ ወሲባዊ ግንኙነት ማድረግ፤
- ✗ ደንበኞችን የእርዳታ ቁሳቁሶችን እንዲሸጡ ወይም በስጦታ እንዲሰጡ ማስገደድ።

## ሪፖርት ማድረድግ ያለብዎት

- ▲ ማንኛውንም አይነት የተጠቃሚዎች ብዝበዛ።
- ▲ ትክክል ያልሆነና አድሎ የሚታይበት ምርጫ ውሳኔዎችን።
- ▲ ሰብአዊ ድጋፍ በሚቀርበበት ጊዜ የሚከሰት ስልጣንን ወይንም ሀላፊነትን ያለአግባቡ የመጠቀም ሁኔታ።
- ▲ ከደንበኞች ጋር የተያያዘ ሚስጥራዊ መረጃዎች አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ይፋ ማድረግ።

# ጥያቄና መልስ

**ጥያቄ:** በስደተኛ ባለቤትነት የሚካሄዱ የንግድ ስራዎች መደገፍ ስለምወድ ከደንበኞቻችን የአንዱን ቤት ለቤት ውስጥ የህጻናት ጥበቃ አገልግሎት እየተጠቀምኩበት ነው። ችግር አለው?

**መልስ:** ፍላጎታቸውና ፍቃዳቸው እስከሆነ ድረስ የIRC ሰራተኞች በተጠቃሚው ባለቤትነት የሚካሄድን ህጋዊ የንግድ ስራ መደገፍ ተቀባይነት ይኖረው ይሆናል። ነገር ግን ለIRC ሰራተኛ የሚሰጠው ዋጋ ወይም ስምምነት ለማህበረ ሰቡ ከሚቀርብበት ጋር አንድ አይነት መሆን አለበት።

---

**ጥያቄ:** አንድ ደንበኛ ስደተኛ ሆኖ ለመመዝገብ የሶስተኛ ወገን መረጃ እየተጠቀመች እንደሆነ ደረስኩበት። ምንም እንኳን ስደተኛ ባትሆንም በጣም በአገርዋ አስከፊ ከሆነ ህይወት እየሸሸች እንደሆነ አውቃለሁ። ይህን መናገር ይጠበቅብኛል።

**መልስ:** አዎ፣ ይህንን «እገዛ ያገኙ» በሚለው በዚህ የስነ ምግባር ደንብ ላይ በተቀመጠው አግባብ መሰረት ይህን ጉዳይ መግለጽ ይኖብዎታል። ነገሩን በሌላ መንገድ ለማየት አለብዎ ከሆነ ግን ትክክል አይሆንም።

---

**ጥያቄ:** ባለፈው ሳምንት የመስክ ጉዞ ላይ ስለነበርን ምሽቱን ያሳለፍነው ከቤታችን እርቀን ነበር። በዚያም ጉዞ አንድ የስራ ባልደረባዬ ከአንድ ሴተኛ አዳሪ ጋር መውጣቱን ለማመን የሚያስችል ምክንያት አግኝቻለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

**መልስ:** ይሄ የIRC ደንብ መጣስ ስለመሆኑ በዚህ የስነ ምግባር ደንብ «እገዛ ያግኙ» የሚለው ክፍል ላይ የተቀመጠ ውን አካሄድ ይከተሉ።

## ጠቃሚ የIRC ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች

- የተጠቃሚዎችን ከብዝበዛና ጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ
- የህፃናት ጥበቃ ፖሊሲ
- የህገ ወጥ ሰዎች ዝውውርን የመዋጋት ፖሊሲ
- ግልጽ / መረጃ ፖሊሲ/
- መረጃ የመስጠት ፖሊሲ
- ተመራማሪዎች የሚጠቀሙበት የተቋም ግምገማ ቦርድ አሰራር

## ለተጨማሪ ንባብ

- የአለም አቀፍ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ንቅናቄ እና የአደጋ እርዳታ በማቅረብ ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች የስነ ምግባር ደንቦች
- የተባበሩት መንግስታት የዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች እና የህ ፃናት የህጻናት መብት ስምምነት
- የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ በወሲባዊ መመሪያ ብዝበዛ እና የተጠቃሚዎች ጥቃት ጥበቃ መግለጫ

# ለለጋሾቻችን ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት

ለጋሾች ስራችንን ለማከናወን የሚያስፈልገንን ሃብት የሚሰጡን በመሆናቸው ይህን ሃብት ኃላፊነት በተሞላበት መንፈስ የመጠበቅ ግዴታ አለብን። ተቋማዊ የሆኑ ለጋሾቻችን ያስቀመጡትን ደንብና ስምምነት ለማክበር እንዲሁም ሌሎች ለጋሾቻችን የሚጠብቁብንን ለማድረግና ደንበኞቻችንን በብቃትና በውጤታማነት ለማገልገል ቁርጠኞች ነን።

## የIRCን አሰራር ደንብ በአግባቡ የሚከተሉት

- ✔ በአፈጻጸም እና በተጠያቂነት ላይ ተግባራዊ የሚሆኑትን የለጋሾችን ደንቦች ሲረዱ
- ✔ የሰዓት መመዝቢያ (Time sheet) የወጪ ሪፖርቶች (Expense Sheet) የቅድመ ወጪ ማወራረጃዎችን እና ሌሎ የፋይናንስ ሰነዶች ትክክለና መሆናቸውን በጥራት መሰራታቸውን ሲያረጋግጡ
- ✔ ለደንበኞች የተሻለ ውጤት ማቅረብ ለማቅረብ የሚችሉ እና ስራቸውንም በተገቢውና በለጋሾች ሕግ መሰረት መስራት የሚችሉ አጋሮችን ሲመርጡ
- ✔ የተቋማዊ ለጋሾቻችንን እና የግለሰቦችን ግላዊና ሚስጥራዊ መረጃዎችን ሲሰጡ
- ✔ በሪፖርት የቀረቡ መረጃዎች ላይ ያሉ ስህተቶችን በተመለከተ ለለጋሾች መረጃ ይስጡ እንዲሁም ግልጽነት እንዲሰፍን ሲጥሩ
- ✔ የእርዳታ መጠየቂያ ሰነዶችን ገንዘብ ማሰባሰብያዎችን የማጠያየቅና ማስተዋወቅ ስራዎችን በሃቀኝት በታማኝነት እና ተግበራዊ ከተደረጉ ሕጎች ሁሉ በሚስማማ መንገድ ሲያከናውኑ
- ✔ ስለIRC እና ስለ ስራው ሲናገሩ ሁልጊዜም እውነተኛና ቀዳሚ ሲሆኑ።

## ማስወገድ ያለብዎት

- ✗ ከልገሳ መመዘኛ መስፈርት ጋር አለመጣጣም ወይም ተገቢ ያልሆነ የፈንድ አጠቃቀም።
- ✗ የሃሰት የስራ ሰዓት፣ የወጪ ወይም የዋጋዎች ሪፖርት።
- ✗ ያሉትን ፈንዶች ያለለጋሾች ፍቃድ ለሌላ ፈንድ ማሰባሰብያ ወጪ ማዋል።
- ✗ የመርሃ ግብር ፍላጎቶችች ዋጋዎች የተጠቃሚዎችን ቁጥር እና ውጤቶችን ማብዛትና በተዛባ መልኩ ማቅረብ።
- ✗ ምርጫዎች ላይ ተጽእኖ ማድረግ፣ ሳይፈቀድ መጠቀም ወይንም በሀገር ውስጥ አጋሮች ላይ ተገቢ ያልሆነ ክትትል ማከናወን።
- ✗ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ተቋሙን ከሌሎች ድርጅቶች አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በማወዳደር ላለመቀበል መሞከር (ማጣመም፣ ማዛቡት)።
- ✗ ሰብአዊ ከሆነ ጉዳይ በስተቀር በማንኛውም ለጋሽ ስም ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ ወይም ምጣኔ ሃብታዊ መረጃዎችን መሰብሰብ።
- ✗ ህገወጥ ከሆኑና በወንጀልና ማጭበርበር ተግባራት ላይ ከተሰማሩ ወይንም እነዚህ አይነት ተግባራትን ከሚፈጽሙ አካላት ጋር ግንኙነት ካላቸው ለጋሾች ስጦታ/ፈንድ መቀበል።

## ሪፖርት ማድረግ ያለብዎ

- ▲ የተሳሳተ የሰዓት፣ ወጪ ወይም ዋጋ ሪፖቶችን።
- ▲ የተጭበረበረ የተጠቃሚዎች ምዝገባን።
- ▲ ስርቆትንና ለእርዳታ የወጡ ንብረቶችን ለሌላ ተግባር ማዋልን።
- ▲ ተገቢ ያልሆነ የሀብት ማሰባሰብ ስራ ማከናወንን።

# ሁኔታ ጥናት

**ጥያቄ:** አንዳንድ የማውቃቸው ወጪዎች ለምሳሌ የአልኮል ወይም የመዝናኛ ወጪዎች የሚፈቀዱ አይደሉም። በፋ ይናንስ ሪፖርት ላይ እንዳይካተቱ እነዚህን ወጪዎች ልዩልዩ በሚለው መደብ ማካተት አልችልም?

**መልስ:** አይቻልም ቀሪ ከሆነ የባጀት መደብ እንዲከፈል ወይም ከማንኛውም የባጀት መደብ የማይፈቀድ ወጪ እንዲ ካፈል ማድረግ በጭራሽ አይኖርብዎትም። በተቋሙ አማካኝት የሚከሰቱ የማይፈቀዱ ወጪዎች የሚሸፈኑት ገደብ ካልተ ጣለባቸው ፈንዶች ብቻ ነው።

---

**ጥያቄ:** የተፈቀደው በጀት ወደ ማለቂያው ሲቃረብ ቀሪውን በጀት ለመጠቀም ብዙ የኮምፒዩተር ግዢ ጥያቄ ቀረበልኝ። የተፈቀደው ገንዘብ ሙሉ ለሙሉ ለመጠቀም ይህን የግዢ ጥያቄ መፈረም (መቀበል) አለብኝ?

**መልስ:** በጭራሽ በአመቱ መጨረሻ የተፈረመውን በጀት ለመጠቀም ብቻ ለበጀት አመቱ መጨረሻ እንደዚህ አይነት ብዙ የግዢ ጥያቄዎችን መቀበል የለብዎትም።

---

**ጥያቄ:** እኔ የምሰራበት መርሃ ግብር ግማሽ ያህሉ ሴቶች እንዲሆኑ አቅዷል። ቡድኑ ግቡ የመታ እንዲመስል ሴት ደንበ ኞችን እየመዘገበ ነው። ነገር ግን በተጨባጭ እየቀረበ ያለው መርሃ ግብር ለባሎቻቸው የሚሆን አገልግሎት እንጅ በቀጥታ ለሴቶች የሚሆን አይደለም። ምን ማድረግ እችላለሁ?

**መልስ:** ይህንን ጉዳይ «እገዛ ያግኙ» በሚለው በዚህ የስነ ምግባር ደንብ ላይ በተገለጸው መሰረት ማንሳት አለዎት።

## ጠቃሚ የIRC ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች

- የሚስጥር አያያዝ ፖሊሲ
- የገንዘብ አጠቃቀም የፊሲካል ታማኝ ነት ፖሊሲ
- ተቋማዊ ስጦታ የማሰባሰብና የመቀ በል ፖሊሲ
- የግልጽ መረጃ ፖሊሲ
- የIRC መርሃ ግብር መመሪያዎች፣ የአ ሰራር ዘዴዎች እና ተግባርን ለማከና ወን የሚያግዙ ሌሎች መመሪያዎች/ ሰነዶች
- የግብዓት ሰንሰለት አሰራር ዘዴዎች / መመሪያዎች
- የስራ መሳሪያዎችንና የመረጃ ጥበቃን የሚገዙ /የሚመለከቱ/ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲዎች
- የፋይናንስ መመሪያዎች



# ለአቅራቢዎቻችን ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት

ለምንገዛቸው ነገሮች ላይ ጥሩ ጥቅም (እሴት) ማግኘት በአቅርቦት ሰንሰለቶቻችን ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ቅንነትና ታማኝነትን ይጠይቃል። ነጻና ፍትሃዊ የአቅራቢዎች ውድድር እንዲኖር፤ በሥነ ምግባርና በኃላፊነት ለመወሰን ያለንን አቋም የሚጋሩ አቅራቢዎችን ለመደገፍ፣ እንዲሁም ለተጎጂዎች ከሚመጣው እርዳታ /ብር/ ያልተገባ ጥቅም በመሻት የሚያጭበረብሩትንና ሙስና የሚሰሩትን ለማስወገድ

## የIRCን አሰራር ደንብ በአግበቡ የሚከተሉት

- ✔ በግዢ ወቅት የሚከሰትን ወይም ማንኛውም ሊከሰት የሚችል የጥቅም ግጭትን፣ ማለትም ግላዊ ፍላጎት ከIRC ፍላጎት ጋር የሚጻረር ሲሆን ማሳወቅ፤
- ✔ ፕሮግራም የሚቀረጽበት እንዲሁም ምርት እና አገልግሎት በሚገዛበት ጊዜ የተሻለ ዋጋ (ጥቅም) መገኘቱን ሲያረጋግጡ።
- ✔ ከግዢ ጥያቄዎች፣ ከጨረታ ማስታወቂያዎች፤ ከጨረታ ትንተናዎች ውልና አቅርቦትን ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች ለመፈ ጸም የግዢ ፖሊሲዎችን ሲከተሉ። (በግዢ ፖሊሲው መሠረት መፈጸሙን ሲያረጋግጡ)።
- ✔ አቅራቢዎችን መረጃ፣ ዋጋ፣ ስምምነቶችና ሁኔታዎች በጥብቅ ሚስጥር ሲይዙ።
- ✔ የአቅራቢዎች መረጃ፣ ያቀረቡት ዋጋና ሁኔታዎች በጥብቅ ሚስጢር ስይዙ።
- ✔ ጨረታዎች በሚሰረዙበት ጊዜ ለአቅራቢዎች የተሟላና ግልጽ የሆነ ማብራሪያ ሲሰጡ።
- ✔ ከግዢ ጥያቄ፣ ከማጽደቅ እና ከማጣራት ጋር ተያይዞ የሚከናወኑት ተግባራት (ኃላፊነትን) መከፋፈል።
- ✔ የመንግስትን ወይም የተቋማዊ ለጋሾችን የግዢ ፖሊሲዎችን « ግራንት ኦፕኒንግ» ስብሰባዎች ላይ።
- ✔ በመንግስት ቁጥጥር የሚደረግላቸው ወይም መላክና ማስመጣት ቁጥጥር ከሚያደረግ አጋር ጋር የተያያዙ ማንኛውም እቃዎች ሶፍትዌር ወይም ቴክኖሎጂ ከመገዛታቸው በፊት የመላክ ፍቃድ አስፈላጊ መሆኑን ወይም ገደቦች መኖራቸውን ሲያረጋግጡ።

## ማስወገድ ያለብዎት

- ✗ በጨረታ ሂደት መረጃዎችን ለአቅራቢዎች እኩል ባልሆነ መስጠት።
- ✗ የአንድ አቅራቢ ሚስጥራዊ መርጃዎችን ለሌላ አቅራቢ ይፋ ማድረግ።
- ✗ የማይገባ ተጽእኖ እንዲፈጥር ወይም ፍትሃዊ ያልሆነ ጥቅም እንድንሰጥ የሚያደርግ የተለያየ ዋጋ ያላቸው እንደ ስጦታ ፤ ውለታ ፤ መዝናኛ ፤ ጉቦ ወይም ጥቅማጥቅም መቀበል።
- ✗ የተቀመጡ መስፈርቶችን የማያሟሉ ፤ ከደረጃ በታች የሆኑ ምርቶች እና አገልግሎቶችን መቀበል።

## ሪፖርት ማድረግ ያለብዎት

- ▲ አድሎ ያለበት የጨረታ ዝርዝር፣ ሰነድ ዝግጅት ወይም የአቅራቢዎች ቅድመ ጨረታ ምርጫን።
- ▲ የጨረታ መጭበርበር፣ መመሳጠር ወይም ሌላ ፍትሃዊ ያልሆነ የአቅራቢዎች አሰራር።
- ▲ ትክክለኛ ያልሆነ የአቅራቢ ብቃት ቅድመ ምርመራ (ፍተሻ)።
- ▲ ለሽብር እንቅስቃሴ፣ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ፣ ከሰብአዊ መብት ረገጣ፣ለአደጋ የተጋለጠ የስራ ሁኔታ ወይም ህገ ወጥ መሳሪያዎች ምርት፣ አቅርቦት ወይም ትራንስፖርት ጋር በተያያዘ ከሚሰሩ ወገኖች ጋር የሚደረግ ስራ።
- ▲ ክፍያን ከተዋዋይ ወገን ውጪ ለመፈጸም የሚቀርቡ ጥያቄዎችን።

## ጥያቄና መልስ

**ጥያቄ፡** አንድ የIRC አቅራቢ የእራት ግብዣ ጥያቄ አቀረበልኝ። ግብዣውን መቀበል እችላለሁ?

**መልስ፡** በእርግጥ የምግብ ግብዣን ከአቅራቢዎች መቀበል ችግር የለውም። ነገር ግን የሚቀርበው የምግብ ግብዣ 1) የተጋነነ እና በሚደረጉ ውሳኔዎች እና ተግባራት ላይ ተጽእኖ ለማድረግ ያልታሰበ 2) በተደጋጋሚ ካልሆነ ለምሳሌ በአመት ከሁለት ጊዜ በላይ 3) የሚካሄደው በሚታወቅና በሚከበር ቦታ ከሆነ 4) የትኞቹንም ህጎች የማይጥስ ከሆነ እና 5) የIRCን ክብር በአደባባይ የማያዋርድ መሆን አለበት።

---

**ጥያቄ፡** የአቅራቢዎች የብቃት ምዘና ሂደት ካከናወንን በኋላ የሳይት ጉብኝታችንን አላካሄድንም (ዘለልነው)። የስራ ባልደረባዬ ይህንን መረጃ እንዲሞላ በሚጠይቀው ቅጽ ላይ እንደጎበኘን አድርጎ ሞላው። ምን ማድረግ አለብኝ?

**መልስ፡** የአቅራቢዎችን ብቃት በተመለከተ የውሸት መረጃ ማቅረብ ተቀባይነት የለውም። «እገዛ ያገኙ» በሚለው ክፍል በዚህ ስነ ምግበር ደንብ ላይ የተቀመጠውን ዝርዝር አሰራር መከተል።

---

**ጥያቄ፡** ከአቅራቢያችን የተቀበልነው ምርት እኛ ካዘዝነው የወረደ ጥራት ካለው እቃ የተሰራ ነው። ምንም እንኳን ጥሩ ምክንያት ባይሆንም አንድ ሰው አጽድቆ ተቀብሎታል ማለት ነው። ይህንን መተው ይገባኛል?

**መልስ፡** በጭራሽ! «እገዛ ያገኙ» በሚለው ክፍል በዚህ ስነ ምግባር ደንብ ላይ በተገለጸው አግባብ ይህንን ጉዳይ ማንሳት አለብዎት። ምንም እንኳን ምርት በአሳማኝ ምክንያት የተለየ ቢሆንም ዝቅ ባለ ደረጃ ምርት ሲቀርብ እንዳላየ ሆኖ ማለፍ አይገባም።

### ጠቃሚ የIRC ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች

- የፊሲካል ታማኝነት ፖሊሲ
- የአለም አቀፍ አስገዳጅ ሰነዶች
- የግዢ መመርያዎች

### ለተጨማሪ ንባብ፡

- የUSAID ዋና ተቆጣጣሪ ጽህፈት ቤት ህትመትና የማጭበርበር ጠቃሚ ምልክቶች
- የ USAID ዋና ተቆጣጣሪ ጽሕፈት ቤት ህትመት። ማጭበርበርን ለመ ከላልና ለመታገል - የመካከለኛው ምስራቅ የሰብአዊ አደጋ ምላሽ አነስ ተኛ መመሪያ



# ለአጋሮቻችን ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት

ከአካባቢያዊ፤ ሃገራዊ እና አለም አቀፍ የማህበረሰብ ድርጅቶች (ሲቪል ሶሳይቲ) እንዲሁም ከመንግስት እና ከግል ድርጅቶች ጋር በአጋርነት መስራት የIRC ተልእኮ ለማሳካት መሰረታዊ ነው።
IRC ሥልታዊ ግቡን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ፤ ፈጣንና ለብዙዎች ዘላቂ ድጋፍ መስጠት የሚያስችል ውጤታማ አጋርነት ለመመስረት (ለመ ገንባት) ቁርጠኛ ነው።

## የIRCን አሰራርን ደንብ በአግባቡ የሚያስኬዱት የሚከተሉትን ሲያደርጉት ነው

- ✔ ተጠያቂነት፣ ግልጽነት፣ መካባበር፣ እኩልነት እና አካታችነትን መሰረት ያደረገ አጋርነት።
- ✔ የሚሰጣቸው ድጋፍ በኃላፊነት የመተግበር አቅም ያላቸው እና የተቀመጠላቸውን የአፈጻጸም ደረጃዎች የሚያሟሉትን አጋሮችን ሲመርጡ እንዲሁም ተገቢው ድጋፍ እንደተደረገላቸው ሲያረጋግጡ።
- ✔ ለመርሃ ግብሮች መሳካት (ውጤት) አጋሮች ለነበራቸው ሚና ሙሉ እውቅና ሲሰጡ።
- ✔ አጋሮች የሚያጋጥማቸውን የደህንነት ስጋት አደንዲያስወግዱ እና እንዲቋቋሙ ድጋፍ ሲያደርጉ።
- ✔ በስራ እንቅስቃሴ ላይ ግልጽ ፣ ነጻ እና በመከባበር ላይ የተመሰረተ የሁለትዮሽ ግንኙነት እንዲኖር ሲያደርጉ።
- ✔ የIRC ፈንድ በህግ፣ በለጋሾች መመዘኛ እንዲሁም በIRC ደንቦች መሰረት ጥቅም ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ተገቢ ውን እርምጃ ሲወስዱ።
- ✔ በተቻለ አቅም በIRC መርሃ ግብሮች እቅድ፤ ዲዛይን፣ አተገባበር እና ግምገማ ወቅት የአካባቢውን አጋሮች ሲያሳትፉ።

## ማስወገድ ያለብዎ

- ✗ ለአጋር ድርጅቶች እና ሰራተኞቻቸው ላይ የማይመችና ክብር የጎደለው ባህሪ ማሳየት
- ✗ ከአጋሮች ጋር በመኖር ግንኙነት ላይ ማንኛውም አይነት ስልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም
- ✗ የአንድ አጋርን ስራ እንደ IRC አድርጎ ማቅረብ

## ሪፖርት ማድረግ ያለብዎ

- ▲ ከአጋር ጋር ባለ ግንኙነት የተከሰተ ወይም ሊከሰት የሚችል የጥቅም ግጭት ሲከሰት።
- ▲ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በተያያዘ የተሳሳተ እና የወገነ ውሳኔ ማሳለፍ።
- ▲ የተጭበረበረ የአጋሮች ምርጫ።
- ▲ እርዳታ ወይም ሃብት በአጋሮች ሲሰረቅ ወይም ለሌላ አላማ ሲውል።
- ▲ የላላ ወይም በቂ ያልሆነ የአጋሮችን አፈጻጸም ወይም ውጤታማነት ቁጥጥር።

# ህያው ኑቅዶሣ

**ጥያቄ:** የአንድ አጋር ድርጅት ኃላፊ እነሱ በአጋርነት ያሽነፉትን የገንዘብ ድጋፍ የዋናው ባጀት ቅጂ ለማየት ጠየቀ። ላሳየው እችላለሁ?

**መልስ:** መረጃውን ለማሳየት ይፈቀድ እንደሆነ የIRC የለጋሾች የሚስጥር ግዴታዎች አስተዳደር ኃላፊውን ወይም የአጠቃላይ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማማከር አለብዎት።

## ጠቃሚ የIRC ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች

- የፊሲካል ታማኝነት ፖሊሲ (የገንዘብ አጠቃቀም ፖሊሲ)
- የIRC አለም አቀፍ ደህንነት ፖሊሲ
- ተጠቃሚዎችን ከብዝበዛና ጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ
- የሰራተኞች የጥቅም ግጭት ፖሊሲ
- መረጃ የመስጠት ፖሊሲ (የግልጽ መረጃ ፖሊሲ)
- የተጋሪ አጋርነት ማኔጅመንት ስርዓት
- የፋይናንስ መመሪያዎች

## ለተጨማሪ ንባብ:

- የአለም አቀፍ ቀይም ጨረቃ ንቅናቄ እና የአደጋ እርዳታ በማቅረብ ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅ ቶች የስነ ምግባር ደንቦች



# ለድርጅታችን ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት

IRC የለጋሾችን መዋጮ ለተጠቃሚዎች /ለተጎጂዎች/ ሰብአዊ ድጋፍ ያውላል። ይህን ለማከናወን IRC የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ጠንካራና ውጤታማ ሆኖ መቀጠል ግድ ይለዋል። የIRC ሃብት እና ንብረት መጠበቅ እና የተቋሙን ፍላጎት ማስቀደም ግድ ይለናል።

## የIRCን አሰራርን ደንብ በአግባቡ የሚከተሉት

- ✔ በስራ የተከሰተን ወይም ሊከሰት የሚችል የጥቅም ግጭትን ማለትም ግላዊ ፍላጎት ከIRC ፍላጎት ጋር የሚጋጭበት ሁኔታ ሲያስወግዱ ሲፈጠር ደግሞ ለአለቃዎ ሲያሳውቁ።
- ✔ የIRCን ሃብት በኃላፊነትና ህጋዊ በሆነ መልኩ ተጠቅሞ እንዲሁም ሃብቱን ከዝርፊያ፣ ከማጭበርበር፤ ከብክነት እና ከጉዳት ሲከላከሉ/ሲጠነቀቁ/ ነገር ግን ራስዎትን ሆነ ሌሎችን ለጉዳት ሳያጋልጡ።
- ✔ ትክክለኛ የሂሳብና ሌሎች ሰነዶችን ሲይዙ።
- ✔ ከግዢ ጥያቄ፣ ከማጽደቅ እና ከማጣራት ጋር ተያይዞ የሚከናወኑት ተግባራት በሚገባ ሲቆጣጠሩ እና ኃላፊነትን ሲከፋፈሉ
- ✔ የባለሙያዎችን ሪፖርት፣ የክፍያ ሰነዶችን፣ የደሞዝ መጠኖችን እና ላልተለመዱ ተግባራት የዋሉ የበጀት ልዩነቶችን ሲቆጣጠሩ።
- ✔ ሚስጥራዊ የሆኑ መረጃዎች በማይመለከተው አካል እንዳይታዩ ወይም ይፋ እንዳይሆኑ ሲጠብቁ።
- ✔ የሰነዶች አያያዝ ወይም አወጋገድ በሰነዶች አያያዝ ፖሊሲዎች መሰረት ሲሆን።
- ✔ ለIRC ሂሳብ ባለሙያ ወይም መርማሪ መረጃ እንዲሰጡ በተጠየቁ ጊዜ ለመተባበር ሙሉ ለሙሉ ዝግጁ ሲሆኑ።

## ማስወገድ ያለብዎት

- ✗ ለግል ጉዳዮት በIRC ያለዎትን ኃላፊነት ወይም መረጃ መጠቀም።
- ✗ ለሌላ መስሪያ ቤት ስራ የIRCን ጊዜ ወይም ንብረት መጠቀም።
- ✗ ሳያሳውቁ ከእርሶ ጋር ከሞያዊ የስራ ግንኙነት ያለፈ ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦች ወይም አካላትን የሚያካትት የመቅጠር ወይም ኮንትራት የመስጠት ውሳኔ ላይ መሳተፍ።
- ✗ የማይገባ ተጽእኖ ለመፍጠር ወይም ፍትሃዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያስገኙ ወይንም ሊያስገኙ የሚችሉ የተለያዩ ዋጋ ያላቸው እንደ ስጦ፣ ውለታ፣ መዝናኛ፤ ጉቦ ወይም ጥቅማጥቅም መፈለግ፣ መቀበል ወይም መስጠት።
- ✗ የሃሰት መረጃና ሪፖርት ማቅረብ (የሰአት መመዝገቢያ፣ ደረሰኞች፣ ንብረት ቆጠራ፣ የሂሳብ መግለጫዎች እና የመርሃግብር ዳታዎች ወ.ዘ.ተ)።
- ✗ የውስጥ ቁጥጥርን ባልተገባ ሁኔታ ማስወገድ ወይም ማለፍ።
- ✗ ያልተፈቀዱ የIT ሃርድዌር ወይም ሶፍትዌር መጫን (መዘርጋት)።
- ✗ ለአለ ወይንም ለሚጠበቅ የሂሳብ ኦዲት ስራ፣ ምርመራ፣ ለፍርድ ቤት ወይም መብት ጥያቄ የሚያገለግሉ መረጃዎችን ማጥፋት።
- ✗ ለIRC የሂሳብ ባለሙያዎች ወይም መርማሪዎች የሃሰት፣ የተሳሳተ ወይንም ያልተሟላ መረጃ መስጠት።

## ሪፖርት ማድረግ ያለብዎት

- ▲ ማጭበርበር፣ ስርቆት፣ ጉቦ እና ዝርፊያ።
- ▲ የIRC የIT ቁሳቁሶች ለግል ጥቅም፣ ለፖለቲካ ስራ፣ ለማስታወቂያ ወይም ገቢ መሰብሰቢያ ወይም ለተከለከለ ጉዳይ መጠቀም።
- ▲ የIRCን መልካም ስም የሚጎዳ ወይም በህዝቡ ዘንድ ያለውን ገጽታ የሚያጎድፍ ማንኛውንም ተግባር

# ጥያቄና መልስ

**ጥያቄ:** የእህቴ ባል ድርጅት IRC መግዛት የሚፈልገውን አገልግሎት ያቀርባል። ለእህቴ ባል እንዲህ አይነት እድል እንዳለ መንገር እችላለሁ?

**መልስ:** እድሉ በይፋ ለህዝብ የተገለጸ ከሆነ ለእህትዎ ባል ስለሁኔታው ሊነግሩት ይችላሉ። ነገር ግን ለእህትዎ ባል ከሌሎች አቅራቢዎች በተለየ ሁኔታ ኢ-ፍትሃዊ ጥቅም እንዲያገኝ ምንም አይነት ነገር መንገር ወይም መስራት የለብዎ ትም። ለምሳሌ IRC ወይም እንዲህ አይነት እድል ለህዝብ ይፋ ያልተደገ መረጃን መናገር የለብዎትም። በመጨረሻም ያህን ዝምድና ለግዢ መምሪያው በማሳወቅ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ከሂደቱ ውጪ መሆን ይኖርብዎታል።

---

**ጥያቄ:** የሆነ ነገር (መረጃ) ያለፈቃድ ይፋ ሊደረግ የማይችል «ሚስጢራዊ መረጃ» ይዞ እንደሆነ እንዴት አውቃለሁ?

**መልስ:** ሚስጥራዊነት የሚወሰነው እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ነው። ጠንቃቃ ይሁኑ።ሁሉም የIRC መረጃዎች የተቋሙ ንብረ ቶች ናቸው። ሁሉም ሚስጥራዊ ሰነዶች ሚስጥራዊ ናቸው ማለት አይደለም። ስለአንድ የተለየ ሰነድ እርግጠኛ ካልሆኑ ይፋ ከማድረግዎ በፊት ከስራ አስኪያጅዎ ወይም ከጽሕፈት ቤቱ ዋና አማካሪ ጋር ይመካከሩ።

## ጠቃሚ የIRC ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች

- የሰራተኞች የጥቅም ግጭት ፖሊሲ
- የገንዘብ አጠቃቀም/ የፊሲካ ታማኝነት ፖሊሲ
- የሚጥር አያያዝ ፖሊሲ
- ተቀባይነት ያለው የኢንፎርሜሽን ቴክሎጂ አጠቃቀም ፖሊሲ
- የአለም አቀፍ አስገዳጅ ሰነዶች አያያዝ ፖሊሲ
- የብዙሃን እና ማህበራዊ ሚዲያ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች
- የIT መሳሪያዎች እና የዳታ ጥበቃ የሚያደርጉ ሌሎች ፖሊሲዎች
- የ «USP» መመሪያ ድጋፍ ለማሰባሰብ





# ለማህበረሰቡ ያለን ትኩረትና ቁርጠኝነት

IRC ለህብረተሰቡ ኃላፊነት የሚሰማው አለም አቀፍ ዜጋ ለመሆን ቁርጠኛ ነው። ከመንግስት፣ ከተቆጣጣሪዎች፣ ከሚዲያ፣ ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር ካለን መስተጋብር ቅንነትን፣ ታማኝነትንና ፍትሃዊነትን መሰረት ያደረገ ነው። በሃገሪቱ እና አብረን በምንሰራው ህብረተሰብ ውስጥ የሕግ የባላይነት እንዲኖር እና ከፍተኛ የስነ ምግባር ደንብ እንዲተ ገበር ድጋፍ እናደርጋለን።

## የIRCን አሰራር ደንብ በአግባቡ የሚከተሉት

- ✔ ከለጋሾች፣ ከመገናኛ ብዙሃን ተቋማት፣ ኦዲተሮች፣ ከተቆጣጣሪ ድርጅቶች ወይም መርማሪዎች ጋር በሚሰሩ ጊዜ እውነተ ኛና የተሟላ መረጃ ሲሰጡ።
- ✔ ስራችንን ከተፈናቀሉ ሰዎች ጥበቃ፣ መረጋጋት እና ከማካተት ጋር የተገናኙ ትልልቅ መነሻዎች ጋር ሲያገናኙት።
- ✔ በስራችን ምክንያት የሚፈጠር ማንኛውም አካባቢያዊ አደጋ ተጽእኖ ሲቀንሱ እና ሲያስተካክሉ።
- ✔ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ራስዎን እንደ IRC አባል እየገለጹ ከሆነ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከዚህ ደንብ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ሲያረጋግጡ።
- ✔ በኢኮኖሚ ማዕቀብ ስር ካሉ አገራት ጋር አብራችሁ ስትሰሩ ወይም የአድማ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከጠቅላላ መማክርት ጽ/ቤት ምክር ሲጠይቁ።
- ✔ ሁሉም የሚድያ ስራዎች፣ ምላሾች፣ ቃለ መጠይቆች እና የህዝብ አድቮኬሲ ስራዎች ጥያቄዎች በተመለከተ ምክር ከአለም አቀፍ ኮሚኒኬሽን ሲጠይቁ።
- ✔ ለሚያደርጉአቸው ሁሉ የማሳመን እንቅስቃሴዎች ከአደቮኬሲ ክፍል አቅጣጫ ሲፈልጉ።

## ማስወገድ ያለብዎት

- ✗ ውሳኔዎች ላይ ተፅእኖ ለማድረግ ወይም ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ለማንኛውም /ከማንኛውም ሰው (የመንግስት ኃላፊን ጨምሮ) ምንም ነገር መስጠት ወይም መቀበል።
- ✗ የመንግስት ድርጅቶች ለሚያቀርቡት የመረጃ ጥያቄ ሀሰተኛ፣ የተዛባ ወይም ያልተሟላ ምላሽ መስጠት።
- ✗ ሰራኞች ለፖለቲካ ወይም ለእርዳታ እንዲያዋጡ ግፊት ማድረግ።
- ✗ አድቮኬሲ ክፍል ያልተሳተፈበት IRCን ወክሎ የሕግ ለውጥ ለማምጣት ድጋፍ ማሰባሰብ እና በማንኛውም የፖለቲካ ዘመቻ ላይ መሳተፍ።
- ✗ የIRC ስራዎችን ሲያከናውኑ ያለዎት ገለልተኝነት (ወይም የገለልተኝነት አቋም) የሚፈታተኑ ወይም የIRC ስም ሊያጎድፍ የሚችሉ ግንኙነቶች።

## ሪፖርት ማድረግ ያለብዎት

- ▲ ማዕቀብ ካልተደረገበት አድማ ጋር ለመተባበር የሚቀርቡ ጥያቄዎች
- ▲ ጤናን፣ ደህንነትን ወይም አካባቢን አደጋ ላይ የሚጥሉ ሁኔታዎችን

## ህጸመ ነቆያሡ

**ጥያቄ፡** አንድ የጉምሩክ ባለስልጣን ኮምፒዩተሮቻችንን የጉምሩክ ሂደቶችን ጨርሰን ለማውጣት ስድስት ሳምንት እን ደሚፈጅ ነገረኝ፡፡ ነገር ግን ትንሽ ገንዘብ «ጉርሻ» ቢሰጠው በአጭር ጊዜ እንደሚጨርሰው ጠቁሞኛል፡፡ ኮፒዩተሮቹን በፍጥ ነት እንፈልጋቸዋለን ግለሰቡ የጠየቀው ገንዘብ ደግሞ ትንሽ ነው፡፡ መክፈል እችላለሁ?

**መልስ፡** በፍጹም መክፈል የለብዎትም የተጠየቀው ክፍያ ኮምፒዩተሮችን ለማውጣት ያስቀመጠው ግልጽና ህጋዊ ተመን ካልሆነ በስተቀር ይህ የተከለከለ ክፍያ (መክፈል የሌለብዎት) ምሳሌ ነው፡፡ ምንም እንኳን የIRC ስራን የማቀዛቀዝ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ ቢኖረውም ድርጅቱ በእንዲህ አይነት ተገቢ ባልሆነ ድርጊት ውስጥ አይሳተፍም፡፡

---

**ጥያቄ፡** የIRC ስራን በሚጠቅም ፖሊሲዎች ላይ እምነት ያላት አንድ የአካባቢው ፖለቲከኛ ለምርጫ እየተወዳደረች ነው፡፡ ከምርጫው ቅስቀሳ የሚያግዙ ወረቀቶችን ማቅረብና የIRC ኮፒ ማሽንን በመጠቀም ወረቀቶችን ለማባዛት ይችላል?

**መልስ፡** አይሆንም የIRC ጊዜ ፤ መሳሪያዎች እና ንብረቶች ለፖለቲካ እንቅስቃሴ መጠቀም አይፈቀድም፡፡

---

**ጥያቄ፡** በማህበራዊ ሚዲያ ላይ IRC ሆን ብሎ የአንድ የተወሰነ ጎሳን እንዳገለለ የሚገልጽ መረጃ አየሁ፡፡ የሁኔታውን ትክክለኛ ገጽታ ለማንኛውም ሰው መግለጽ እችላለሁ?

**መልስ፡** በራስዎት ውሳኔ IRCን ወክሎው በማህበራዊ ክርክር መሳተፍ የለብዎትም፤ ይህንን ጉዳይ እንዴት መስተናገድ እንዳለበት ለሚወስኑት ለአለቃዎ ወይም ለIRC ኮሚኒኬሽን ቡድን ማሳወቅ አለብዎት፡፡

### ጠቃሚ የIRC ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች

- የጸረ ጉቦ ፖሊሲ
- የጸረ ህገ-ወጥ ገንዘብ ዝውውር ፖሊሲ
- የፊሲካል ታማኝነት ፖሊሲ
- የኢኮኖሚ እገዳ እና የጸረ ሽብርተኝነት አተገባበር ፖሊሲ
- የውጭ ንግድ ቁጥጥር ፖሊሲ
- የፀረ- አድማ ፖሊሲ
- የአካባቢ ፖሊሲ
- የግዢ መመሪያ



# እርዳታ ሲፈልጉ

**ይህ ክፍል የስነ ምግባር ደንቡ በሁሉም IRC የሥራ ክፍሎች በተገቢው ሁኔታ እንዲተገበር ያሉትን ሃብቶች (መንገዶች) የሚገልጽ ነው።**

## የስነ ምግባር አጣብቂኝ ጉዳዮችን መለየት

አንድ ውሳኔ ከመወሰንህ ወይንም እርምጃ ከመውሰድህ በፊት የነገሩን ስነ ምግባራዊ ገጽታዎች ማጤንና ራስዎን መጠየቅ አለብዎ።

- **ውሳኔው ወይም ድርጊቱ ከIRC ደንብ እና ሌሎች ግዴታዎች ጋር ይጣጣማል?**
- **ውሳኔው ማንን ሊነካ (ተጽእኖ ሊያሳድር) ይችላል?**
- **ተጨማሪ ምክር ወይም እውቀት ይረዳ ይሆን?**
- **ይህ ውሳኔ ይፋ ቢሆን ነገሩን ለስራ ባልደረቦች ወይም መርማሪዎች ለማብራራት ምቾት ይሰማኝ ይሆን?**
- **ውሳኔዬ ገለልተኛ ነው ወይስ ተጨባጭ ውሳኔ እንዳላደርግ በውጤቱ ላይ እራሴን የሚመለከት ጉዳይ አለ?**

## መናገር ያለብዎት

የስህተት ስራ አንዱ አስከፊ ገጽታው ሰዎች ነገሩን በሌላ መልኩ ማየታቸው ነው። በስራዎ ላይ ተግባራዊ የሚደረጉትን ሥነ ምግባራዊ እና ህጋዊ ግዴታዎች ከማወቅ በተጨማሪ እንዲገልጹ፣ እንዲያሳውቁ የሚ ጠበቅብዎ፡

- **ትክክለኛ አተገባበር መሆኑ እርግጠኛ ካልሆኑ ምክር ሲያስፈልግዎ።**
- **ያልተመቹህ ድርጊቶች ወይም ውሳኔዎች ሲኖሩ።**
- **ከሚከተሉት ወገኖች አንዱ ከIRC ስራ ጋር በተገናኘ በህገወጥ ወይም ኢ-ስነ ምግባራዊ የሆነ ጉዳይ መፈጸሙን አውቀው ወይም ጠርጥረህ ከሆነ።**
  - **የIRC ስራ አስኪያጆች፣ ሰራተኞች፣ ጥቅማጥቅም የሚያገኙ ሰራተኞች ወይም በጎ ፍቃደኞች ፤ አቅራቢዎች**
  - **አጋሮች ወይም በዋና ኮንትራክተሮች የተቀጠሩ ሌሎች ኮንትራክተሮች ፤**
  - **ወኪሎች፣ አማካሪዎች ወይም በIRC ስም የሚሰሩ ተወካዮች።**





## ቅሬታ የሚቀርብባቸው መንገዶች

IRC ሰራተኞች ምክር ለማግኘት ወይም ቅሬታቸውን ሪፖርት ለማድግ የሚችሉባቸው በርካታ መንገዶች አሉት። የሚመችህን መንገድ መምረጥ አለብህ ነገር ግን ለጉዳዩ ቅርበት ወይንም ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸው የስራ ባልደረቦችዎ፣ ተቆጣጣሪዎ ወይም በአቅራቢያዎ ያሉት አመራሮች ሊረዱህ ዝግጁ ናቸው። ‹‹ናሙና ጉዳዮች›› በሚለው አውድ ስር የተዘረዘሩት ግብዓቶች እነዚህን ያካትታል (ከታች ይመልከቱ)፡



| ናሙና ጉዳዮች | ግምት ውስጥ የሚገቡ ግብዓቶች |
|---|---|
| **አካባቢያዊ የስራ ጉዳዮች** | **ተቆጣጣሪዎች/ የአካባቢ ስራ-አስኪያጆች** |
| **የስራ ቦታ አለመስማማት (የስራ ምደባ፣ የስራ አፈጻጸም ግምገማ፣ ካሳ፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ከተቆጣጣሪዎች ወይም ባልደረቦች ጋር የሚኖር ግጭት)** | **የሰው ሃብት (HR)** |
| **የIRC ሰራተኞችና ሃብት ደህንነት** | **ደህንነት** |
| **የፋይናንስ ሪፖርቲንግ፣ አካውንቲንግ፣ ታክስ ሪፖርቲንግ፣ ሰነዶችና መረጃዎች** | **ፋይናንስ** |
| **ከለጋሾች ጋር የሚደረግ የሃብት ማሰባሰብ ወይም አተገባበር ስራ ወይም የልገሳ መመዘኛዎች** | **የሽልማት ማኔጅመንት ክፍል** |
| **የግዢ ወይም የአቅርቦት ሰንሰለት ጉዳዮች** | **አለም አቀፍ የአቅርቦት ሰንሰለት** |
| **ሕጋዊ ወይም የፖሊሲ አተረጓጎሞች** | **የዋና አማካሪ ጽሕፈት ቤት** |
| **ከዚህ በላይ ያልተገለጹ የስነ ምግባር ደንብ ጉዳዮች ወይም ከመጀመሪያው ምክክር በኋላ እልባት ያላገኙ ጉዳዮች** | **የስነ ምግባርና ደንብ ማክበር ክፍል** |

የቀረበ ቅሬታ የIRC ደንብ ጥሰት የሚያመለክት ከሆነ ሁሉም ክፍሎች ከስነምግባርና ደንብ ማክበር ክፍል ጋር አብሮ የመስራት ኃላፊነት እንዳለባቸው ልብ ይበሉ።

# የቅሬታ አቀራረብ

ሥለጉዳይዎ ከቅርብ አለቃዎ ወይም ስራ አስኪያጅ ጋር ለማውራት ጥሩ ስሜት ይሰማዎታል?

አዎ

አለቃህን ወይም ስራ አስኪያጅህዎን አናግሩ

የለም

ሌላ የአካባቢ ወይም የቀጠና ስራ አስኪያጅ ማናገር ይችላሉ

አዎ

ሌላ ስራ አስኪያጅ አናግሩ

የለም

ከድጋፍ ሰጪ ክፍሎች ጋር መገነኘት ትችላለህ (ለምሳሌ የሰው ሀብት፣ የደህንነት፣ የፋይናንስ እና የዋና ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ወ.ዘ.ተ)

አዎ

ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች ማግኘት

የለም

ኢሜይል integrity@rescue.org ወይም የስነ ምግባርና ደንብ ማክበር ቀጥታ ስልክ ተጠቀም

አዎ

(ቀጣዩን ገጽ ይመልከቱ)

**Integrity@rescue.org**

ይህን የኢሜይል አድራሻ የሚቆጣጠረው ኒውዮርክ የሚገኘው ECU ነው።
ጥያቄዎች እና ሌሎች ጉዳዮችዎን ወደዚህ ኢሜይል አድራሻ መላክ ይችላሉ።

## የስነ ምግባርና ቅሬታ ማቅረቢያ ነጻ ስልክ መስመር

የስነ ምግባርና ቅሬታ ማቅረቢያ ነጻ የስልክ መስመር የሚያገኙት

- **ሌሎች የግንኙነት መንገዶች መጠቀም ሳይመችዎ ሲቀር።**
- **ሌሎች የግንኙነት መንገዶች የማይፈጥኑና የማይሰሩ ሲሆኑ።**
- **ጉዳይዎን ማንነትዎን ሳይገልጹ ሪፖርት ማድረግ ሲፈልጉ።**

ነጻውን የስልክ መስመር የሚቆጣጠረው ሶስተኛ ወገን እና ገለልተኛ የሆነ አካል የሆነው Ethics Point ሲሆን የስልክ ቁጥሮችን ወይም የኮፒዩተር IPአድራሻን አይ መዘግብም። ለ24 ሰዓት ሳምንቱን በሙሉ በተለያዩ ቋንቋዎች ይሰራል። ለማንም ከIRC ጋር ለሚሰራ ሰው (ሰራተኞች ፣ ደንበኞች ፣ አቅራቢዎች ወይም አጋሮች) እን ዲጠቀሙ ዝግጁ ነው።

የስልኩ የተለያዩ አማራጮች የሚጠቀሙ ከሆነ ከአጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚኖር ዎን ጠያቄ ወይም ማብራሪያ ከ Ethics Point የሰለጠነ ባለሙያ በዝርዝር ያስረ ዳዎታል። ጉዳይዎን በዝርዝር ይያዛል። ዝርዝሩ ለተጨማሪ ምላሽ ወደ IRC የስነ ምግባርና ትግበራ ክፍል ይላካል።

**EthicsPoint በቴሌፎን ወይም ኦንላይን ማግኘት ይቻላል:**

**ስልክ**
**ከአሜሪካ ውጪ**
**+1 (503) 352-8177**
**(ነፃ የስልክ ጥሪ)**

**አሜሪካ ውስጥ**
**(866) 654-6461**

**ኦንላይን**
**Irc.ethicspoint.com ይገብኙ እንዲሁም መመሪያውን ይከተሉ**

## ማንነትን አለመግለጽ እና ሚስጥራዊነት

ሃሳዎን በሚገልጹበት ጊዜ ስምዎን እንዲገልጹ ይበረታታሉ። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ለጉዳይዎ መልስ የሚሰጥዎ ወገኖች ነገሩን በዝርዝር ለማየት እንዲችሉ ተጨማሪ መረጃዎች ሲፈልጉ ለመጠየቅ ይረዳቸዋል። ስምዎን መስጠትዎ ሌላው ጥቅሙ እርሶ ወደ በቀል አለመግባትዎን ለማረጋገጥ ይረዳል። (አንዳንድ ጊዜ ማንነትዎን ለመግለጽ በህግ የሚ ገደዱባቸው ወይም ጉዳይዎን በደንብ ለመመርመር አስፈላጊ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች አሉ)።

የነጻ ስልክ መስመር ሲጠቀሙ ማንነትዎን መግለጽ ከፈለጉ IRC ሚስጥራዊነት ይጠብቃል። ነገር ግን ማወቅ ያለባ ቸው የሰጡት መረጃ በቀጥታ ለሚደርሳቸው ሰዎች ብቻ እንዲያገኙት ይደረጋል።

ማንነትዎን ሳይገልጹ ሪፖርት ማድረግ በሚፈልጉ ጊዜ የሚሰጡት መረጃ በዝርዝር ቢሆን ጠቃሚ ነው። Ethics Point የራስዎን ብቻ የሆነ መለያ ቁጥር ይሰጥዎታል። እርስዎም በየጊዜው ይህንን መከታተልና ከመርማሪ ቡድኑ ለሚቀርቡልዎ ጥያቄዎች መልስ መስጠት አለብዎ። ለመርማሪዎች በቂ መረጃ የማይቀርብባቸው ጉዳዮች ሊዘጉ ይችላሉ።

IRC ግለሰቦች ማንነታቸውን ሳይገልጹ ጉዳያቸውን ሪፖረት ማድረጋቸውን ይቀበላል። ነገር ግን ነጻ የስልክ መስመሩን በማይታወቅ ምክንያት የውሸት አቤቱ ማቅረቢያ አታድርጉት ይላል፡ ማንነት ሳይገለጽ የሚቀርቡ ሃሰተኛ ውንጀላዎች የነፃ ስልክ መስመሩን ተአማኒነት ይጎዳዋል።

## የፀረ በቀል ፖሊሲ

IRC በቅን ልቦና እውነተኛ ጥቆማ በሰጡ እና በምርመራው በተሳተፉ ግለሰቦች ላይ የሚከሰቱ የበቀል እርምጃዎችን አይታገስም (ጥቆማው በተጨባጭ መረጃ መደገፍ ባይቻል እንኳ)።

በምንም አይነት ኃላፊነት ወይም ስራ ልምድ ያለ ሰራተኛ ጥቆማ በሰጡ ወገኖች ላይ የበቀለ ተግባር ላይ ተሳትፈው ቢገኙ ከስራ እስከ መባረር ሊያደርስ የሚችል ዲስፕሊን እርምጃ ይወሰድባቸዋል። ለበቀል እርምጃ የተጋለጥኩ ነኝ ብለው ካሰቡ ከነፃ የስልክ መስመሩ አገ ልግሎት ድጋፍ ለማግኘት ግንኙነት መፍጠር ይኖርብዎታል።

IRC ስራ አስኪያጆችና ሰራተኞች ጥሰቶችን በገዛ ራሳቸው እንዲያሳውቁ ያበረታታል። እንዲሁም እንደሁኔታው በራስ ፈቃድ የሚደረግ ማሳወቅ የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወሰድ እንደማቅለያ ሊወሰዱ ይችላል።

## ፈጣን ምላሽ መስጠት

IRC ሁሉንም ጉዳዮች በአግበቡ በአትኩሮት ይመለከታል። እንዴትም ይቀረቡ እርምጃ ይወስዳል። ባቀረቡት ጥቆማ ምክንያት የሰዎች ግላዊ ህይወት ተነክቶ ሊሆን ስለሚችል IRC የምርመራውን ዝርዝር ውጤት ወይም በምላሹ የተወሰዱ እርምጃዎችን ላይነግርዎ ይችላል። የሚቻል ሲሆን ጉዳይዎ የደረሰበትን ደረጃ እንገልጻለን በዚህም ጉዳይህ ተገቢውን ትኩረትና ምላሽ እንደሚያገኝ ያውቃሉ። የIRC ከፍተኛ አመራር አባላት እና የዳይሬክተሮች ቦርድ የኦዲት ኮሚቴ ጉዳዮችን አፈጻጸም ይከታተላሉ።

## ጥያቄና መልስ

**ጥያቄ: የIRC አሰራር ደንብ ሲጣስ ያየሁ ይመስለኛል ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ አይደለሁም በኋላ ተሳስቼ ሆኖ ሊሆን ስለሚችል ሪፖርት ማድረግ አልፈኩም። ምን ማድረግ አለብኝ?**

**መልስ: ምንም እንኳን ሁሉም መረጃዎች ባይኖርዎም ጉዳይዎን ወዲያውኑ ሪፖርት ያድርጉ፣ የሚመ ለከተው ባለሙያ ጉዳዩን በመመልከት የተጣሰ ጉዳይ መኖር አለመኖሩን ይወስናል። አሰራር ተጥሷል የሚል እምነት ኖሮዎ በቀና ልቦና ሪፖርት ማድረግዎ ትክክለኛ ነገር ነው ያደረጉት።**

# ሕግ ማስከበር

በምንም አይነት ኃላፊነት ወይም ልምድ ያሉ ሰራተኞች የIRC ስነ ምግባር ደንብ ወይም መሰረታዊ ፖሊሲዎችን ከጣሱ ከስራ እስከ መባረር የሚያደርስ የዲስፕሊን እርምጃ ይወስድበቸዋል። የሚከተሉት ባህሪያት የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድ የሚያደርጉ ተግባራት ይገኙበታል፡

- **የስነ ምግባር ጥሰት**
- **ሌሎች የስነ ምግባር ጥሰት እንዲፈጽሙ መምራት ወይም ማበረታታት**
- **የተፈጸሙ ወይም የሚጠረጠሩ የደንብ ጥሰቶች ሪፖርት አለማድረግ**
- **በኦዲት ወይም በምርመራ ስራ ጣልቃ መግባት**
- **በኦዲት ወይም በምርመራ ጊዜ አለመተባበር ወይም ሀሰተኛ መረጃ መስጠት**
- **ሪፖርት ወይም ጥቆማ ባደረጉ ሰዎች ላይ በቀል መፈጸም**

የህግ ወይም የደንብ ጥሰት የህግ ተጠያቂነት በእርስዎ፣ በስራ ባልደረቦች፣ በIRC ወይም በአጋሮች ወይም በአቅራቢዎቹ ላይ የሚያስከትል ሲሆን ለሚከተሉት ይዳርጋል።

- **ቅጣቶች**
- **እገዳ**
- **መባረር**
- **እስር**

IRCን በመወከል የሚሰሩ ሰዎች ሁሉ ይህንን የስነ ምግባር ደንብ በፊርማ በማጽደቅ፣ እንደተረዱትና እንደሚገዙበት ያረጋግጣሉ። እያንዳንዱ ሰራተኛ በIRC ስራ በሚጀምርበት ጊዜና በህግ አስገዳጅ ሲሆን በየአመቱ የሚፈረም ይሆናል።





# ማስታወሻ

INTERNATIONAL RESCUE COMMITTEE

**አለምአቀፍ ዋና መቀመጫ**

122 East 42nd Street
New York, New York 10168-1289
አሜሪካ
ስልክ፡ + 1 212 551 3000
ፋክስ፡ + 1 212 551 3179